የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

**OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE**

| | | |
|---|---|---|
| 16 ኛ ዓመት ቁጥር 3<br>16 th Year No. 3 | | ሐረር የካቲት 21 ቀን 2003 ዓ/ም<br>HARAR, Feb 28, 2011 |
| ያንዱ ዋጋ ብር 2.80<br>Unit Price Birr 2.80 | በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖ.ሣ.ቁ. 952<br>P.O.Box 952 |

ማውጫ


አዋጅ ቁጥር 98/2003 ዓ/ም

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብርን ለመወሰን የወጣ አዋጅ.................. ገጽ 753


## አዋጅ ቁጥር 98/2003

## የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብርን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

በሐረሪ ህዝብ ክልል እስካሁን በስራ ላይ ያለው የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ ሕግ ከኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ጋር የማይጣጣም ከመሆኑም በላይ በእርሻ ስራ ገቢ ላይና ለገጠር መሬት መጠቀሚያ የሚከፈለው ግብር የአርሶ አደሮችን የመክፈል አቅምና የእርሻ መሬት በኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን ድርሻ ከግምት ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ፣

ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ እንዲቻል ሚዛናዊ የሆነ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር አከፋፈል ስርአት በመዘርጋት ገቢን ለማሳደግ የሚያስችል አዲስ ስርአት በማስፈለጉ፣

በተሻሻለው የሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት ሕገ መንግስት አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሰ) እና (አ) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

   ይህ አዋጅ "በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 98/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "የገጠር መሬት" ማለት አርሶ አደሩ ለእርሻ ስራ አገልግሎት የሚጠቀምበት ወይም በየትኛውም አካባቢ በአርሶ አደር ይዞታ ስር ያለ መሬት ማለት ነው፡፡

2. "አርሶ አደር" ማለት በገጠር የመሬት የይዞታ መብት ያለው እና ከመሬቱም በሚያገኘው ገቢ እራሱን ወይም ቤተሰቡን የሚያስተዳድር ሰው ነው ፡፡

3. "ክፍያ" ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የሚጠየቅ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ ነው፡፡

4. "የገቢ ግብር" ማለት የመሬት ይዞታ መጠንን መሰረት በማድረግ ከእርሻ ስራ በሚገኝ ገቢ ላይ ተወስኖ የሚከፈል ግብር ነው፡፡

5. "የመሬት ይዞታ" ማለት በአንድ አካባቢ ወይም በተለያዩ ቦታዎች ሆኖ በአርሶ አደር ስም የተመዘገበና ለእርሻ ስራ የተያዘ መሬት ሲሆን የጓሮ እርሻን ይጨምራል፡፡

6. "በምግብ ዋስትና የታቀፉ አርሶ አደር " ማለት የክልሉ መንግስት ባወጣው የምግብ ዋስትና መርሃ ግብር የታቀፉ አርሶ አደር ቤተሰብ ማለት ነው፡፡

7. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ ሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

8. "ግብር ሰብሳቢ" ማለት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ እና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር እንዲሰበስብ የቀበሌ መስተዳደር ጽህፈት ቤት ለሚወክለው ሰው ባለሥልጣኑ እውቅና የሰጠው ሰው ነው፡፡

9. "ባለስልጣን" ማለት የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የገቢዎች ባለስልጣን ነው፡፡

10. "መስተዳደር ም/ቤት" ማለት የክልሉ መንግስት ከፍተኛ የህግ አስፈፃሚ አካል ነው፡፡

11. "መንግስት" ማለት የሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት ነው፡፡

12. "ቀበሌ መስተዳድር" ማለት በአዋጅ ቁጥር 74/2000 አንቀጽ 3(1) መሰረት የተቋቋመ የቀበሌ መስተዳድር ነው፡፡

13. "ማህበራዊ ፍርድ ቤት " ማለት በአዋጅ ቁጥር 74/2000 አንቀጽ 22(1) መሰረት የተቋቋመ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ነው ፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና ስለእርሻ ሥራ ገቢ ግብር

### 3. ስለገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና ስለ እርሻ ሥራ ገቢ ግብር አከፋፈል

ማንኛውም አርሶ አደር ለያዘው የገጠር መሬት አገልግሎትና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር በዚህ አዋጅ አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ በተቀመጠው ሰንጠረዥ መሰረት የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

### 4. ስለገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር ክፍያ ተመን

1. በሐረሪ ህዝብ ክልል የሚገኝ ማንኛውም አርሶ አደር የሚከፍለው ዓመታዊ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር ተመን እንደሚከተለው ነው፡፡

**ሰንጠረዥ አንድ**

| ተ.ቁ | የመሬት ይዞታ መጠን በሄ/ር | ከገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ በብር | ከእርሻ ስራ ገቢ ግብር በብር | ድምር ብር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከ0.5 ሄክታር | 15 | 25 | 40 |
| 2 | ከ0.5 -1 ሄክታር | 20 | 35 | 55 |
| 3 | ከ1 -1.5 ሄክታር | 25 | 50 | 75 |
| 4 | ከ1.5-2 ሄክታር | 30 | 70 | 100 |
| 5 | ከ2-2.5 ሄክታር | 35 | 95 | 130 |
| 6 | ከ2.5-3 ሄክታር | 40 | 130 | 170 |
| 7 | ከ3 ሄክታር በላይ | 50 | 150 | 200 |

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ መንግስት ባወጣው የምግብ ዋስትና መርሃ ግብር የታቀፉ አርሶ አደር ቤተሰብ የሚከፍለው ዓመታዊ የገጠር መሬት መጠቀሚያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር ክፍያ ተመን እንደሚከተለው ነው፡፡

## ሰንጠረዥ ሁለት

| ተ.ቁ | የመሬት ይዞታ መጠን በሄ/ር | ከገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ | የእርሻ ስራ ገቢ ግብር በብር | ድምር ብር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከ0.5 ሄክታር በታች | 10 | 20 | 30 |
| 2 | ከ0.5 -1 ሄክታር | 15 | 30 | 45 |
| 3 | ከ1 - 1.5 ሄክታር | 20 | 40 | 60 |
| 4 | ከ1.5-2 ሄክታር | 25 | 55 | 80 |
| 5 | ከ2-2.5 ሄክታር | 30 | 75 | 105 |
| 6 | ከ2.5-3 ሄክታር | 35 | 105 | 140 |
| 7 | ከ3 ሄክታር በላይ | 40 | 140 | 180 |

### 5. የክፍያና ግብር ተመን ስሌት

1. የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ እና እርሻ ስራ ገቢ ግብር መጠን ተሰልቶ የሚወሰነው እያንዳንዱ አርሶ አደር ባለው የመሬት ይዞታ መጠን ላይ ተመስርቶ ይሆናል፡፡
2. በተለያዩ ቦታዎች የእርሻ መጠቀሚያ ቦታ ያለው አርሶ አደር የእርሻ መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር የሚከፈለው የእያንዳንዱ መሬት ተደምሮ በሚገኘው ድምር ውጤት መሰረት ተሰልቶ በሚገኘው መጠን ይሆናል ፡፡

### 6. ስለ ግዴታዎች

ማንኛውም አርሶ አደር በዚህ አዋጅ አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ስር የተወሰነውን ክፍያ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 ስር በተደነገገው ጊዜ ገደብ ውስጥ ለግብር ሰብሳቢ አካል የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

### 7. ስለገቢ ግብር መሰብሰቢያ ጊዜ

በዚህ አዋጅ መሰረት የሚጠየቅ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ እና እርሻ ስራ ገቢ ግብር ክፍያ የሚሰበሰበው በበጀት ዓመቱ ከጥቅምት 1 እስከ ሚያዚያ 30 ባለው ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## የግብር አስገቢ አካላት ሥልጣንና ተግባር

### 8. የባለስልጣኑ ስልጣንና ተግባር

1. ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚወጡ ደንቦችን በስራ ላይ የማዋል እና የማስፈፀም ኃላፊነት የባለስልጣኑ ይሆናል፡፡
2. በግብር ከፋይ አርሶ አደር ከፍተኛ የተፈጥሮ አደጋ ወይም ችግር፣ ጥፋት ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር በዚህ አዋጅ መሰረት ግብር ከፋዩን አርሶ አደር ከግብር ለአንድ የግብር መክፈያ ዘመን ሊሰርዝለት ይችላል ፡፡
3. ማንኛውም የቀበሌ መስተዳድር ግብር ሰብሳቢ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 መሰረት የሚሰበስበውን ግብር ገቢ መደረጉን በበላይነት ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፡፡
4. በየቀበሌው የተመደቡ ግብር ሰብሳቢዎች ወደ ግብር አሰባሰቡ ሂደት ከመግባታቸው በፊት ባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ተገቢው የአሰራርና የአፈፃፀም መመሪያ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
5. የገንዘብ አያያዝና አጠባበቅ ላይ ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ አስፈላጊውን መመሪያ ይሰጣል፡፡

### 9. ስለ ቀበሌ መስተዳድር ኃላፊነት

1. እያንዳንዱ ቀበሌ መስተዳድር በዚህ አዋጅ መሰረት የደረሠውን ወይም የተላከለትን የአርሶ አደሮች ዝርዝር እንደደረሰው ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ለባለስልጣኑ ያስተላልፋል፡፡
2. ማንኛውም የቀበሌ መስተዳደር ጽ/ቤት በቀበሌው ውስጥ የሚኖሩ ግብር ከፋይ አርሶ አደሮች ስም ዝርዝር ከመሬት ይዞታ ስፋትና መጠናቸው ጋር በየበጀት ዓመቱ ከመስከረም 30 ቀን በፊት ለባለስልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡
3. በየጊዜው ግብር የከፈለና ያልከፈለውን የመለየት ሥራ ያከናውናል ለባለሥልጣኑ መረጃውን ያስተላልፋል፡፡

**10. ስለ ውሳኔ አፈፃፀም**

ማንኛውም አርሶ አደር የተወሰነበትን የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ የገቢ ግብር በዚህ አዋጅ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ የመክፈያው ጊዜ ካለፈበት ቀን ጀምሮ በማናቸውም ጊዜ ባለስልጣኑ በሚመለከተው የቀበሌ መስተዳደር ማህበራዊ ፍርድ ቤት ክስ ሊመሰርትበት ይችላል፡፡

**11. ደረሰኝ ስለመስጠት**

1. ማንኛውም አርሶ አደር በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚፈፅመው የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር ከግብር ሰብሳቢው ህጋዊ ደረሰኝ የማግኘት መብት አለው፡፡
2. በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከፈል የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር የሚሰበሰበው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ባዘጋጀው ወይም በሚያዘጋጀው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብቻ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**12. ስለመቀጫ**

ማንኛውም አርሶ አደር በዚህ አዋጅ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ሣይከፍል ከቀረ ክፍያው ወይም ግብሩ ባዛገየበት በእያንዳንዱ ወር ብር 5 (አምስት ብር) ይከፍላል፡፡ ሆኖም የመቀጫው መጠን ከዋናው ግብር መብለጥ የለበትም፡፡

**13. ስለ አበል**

የቀበሌ መስተዳደር በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚሰበስበው ገንዘብ ውስጥ ሁለት በመቶ /2%/ በኮሚሽን መልክ ይሠጠዋል፡፡ ክፍያውን በተመለከተ ደንብና መመሪያ ሊወጣ ይችላል፡፡

**14. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅና በአዋጁ መሰረት የሚወጣውን ደንብ ወይም መመሪያ በስራ ላይ በማዋል ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**15. ስለ ወንጀል ቅጣት**

ይህንን አዋጅ ወይም በአዋጅ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ወይም መመሪያ የተላለፈ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት ይቀጣል፡፡

**16. ተፈፃሚነት ስለማይኖረው ህግ**

1. ከዚህ በፊት ሲያገለግል የቆየው የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር ይህ አዋጅ በስራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ህግ፣ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**17. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚረዱትን ደንቦች የማውጣት ስልጣን ይኖረዋል፡፡
2. ይህንን አዋጅና በአዋጁ መሰረት የሚወጡትን ደንቦች ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ባለስልጣኑ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**18. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሐረር - የካቲት 21 ቀን ¸ 2003 ዓ.ም

**ሙራድ አብዱልሃዲ**

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት